# BNB LEARNING CEMTRE REGOSTRATION FORM

## የ BNB ትምህርት ማዕከል የተማሪዎች መመዝገቢያ ፎርም

### ሀዋሳ፣ ኢትዮጵያ

| የተማሪው ፎቶ ግራፍ | | የወላጅ ፎቶ ግራፍ |
|---|---|---|

ቀን ____________________

የተማሪው ሙሉ ስም ________________________________

የትውልድ ዘመን፣ ________ቀን_________ ወር _______ ዓ.ም

ዕድሜ _______ ፆታ ☐ ወ ☐ ሴ

የነበረበት ት/ቤት ______________________________ የሚገባበት ክፍል ________

**የወላጅ /የቅርብ ተጠሪው/ አድራሻ**

የመጀመሪያ ተያዥ ስም ______________________________አድራሻ __________ስልክ ____________

የሁለተኛ ተያዥ ሰም ________________________________አድራሻ___________ስልክ_____________

<u>የBNBት/ማዕከል ህግና ደንብ</u>

<u>ለ6ኛ፣ለ8ኛ እና 12ኛ ክፍል ተማሪዎች</u>

1. ማጠናከሪያ ት/ት ዓመቱን ሙሉ የሚሰጠውን በአግባቡ የመከታተል እና ለአገልግሎት የሚያስፈልገውን ክፍያ የመክፍል ግዴታ አለበት/ባት፡፡
2. ማጠናከሪያ ት/ት ማለት በት/ቤታችን መደበኛ ት/ት መሆኑን ማወቅ፡፡
3. ለ3ቱም (6፣8 እና 12) የክፍል ደረጃዎች በአንደኛ መንፈቀ ዓመት የሚያስመዘግቡት አማካይ

ውጤት ከ65 በታች ከሆነ ተማሪው ወይም ተማሪዋ ክልላዊ እና ብሔራዊ ፈተናዎችን አይፈተኑም፡፡

የBNB ትምህርት ማዕከል ህግና ደንብ እንደሁኔታው ቀላል ጥፋቶችና ከባድ ጥፋቶች በመባል በሁለት ተከፍሎ ከነቅጣቶቹ ጋር እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርቧል፡፡

1. <u>ቀላል ጥፋቶች</u>

1.1 ማርፈድ፣
1.2 በትምህርት ሰዓት ግቢ ውስጥ መዘዋወር፣
1.3 ለወላጅ የተላከውን መልዕክት ያለማድረስ፣
1.4 የትምህርት መሣሪያዎችን፣ የደንብ ልብስና የመመገቢያ ዕቃ በየቦታው መጣል፣
1.5 ወረቀት በክፍልም ሆነ በት/ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ መጣል፣
1.6 በት/ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ በተከለከሉ ቦታዎች መዘዋወር፣
1.7 በትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ ጀላቲ መምጠጥ፡፡

2. <u>በቅድም ተከተል የሚወሰዱ የቀላል ጥፋቶች ቅጣት</u>

2.1 ምክርና ማስጠንቀቂያ መስጠት፣
2.2 ለወላጅ ማሳወቅና ማስፈረም፣
2.3 ከትምህርት ገበታ ለተወሰነ ጊዜ ማገድ፣
2.4 ካልታረመ ወይም መሻሻል ካላሳየ ከት/ቤት ማባረር፡፡

## 3. ከባድ ጥፋቶች

3.1 በት/ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ በግልም ሆነ በቡድን ፀብ፣ ረብሻ፣ ድብድብ መፍጠር፣ ወዘተ፣

3.2 በት/ቤቱ የሚገኙ ተማሪዎችን፣ ሠራተኞችንና መምህራንን መደባደብ፣ መሳደብ ወይም ማንጓጠጥ ፣ ወዘተ፣

3.3 ከትምህርት መሳሪያ ውጪ ስለታም /ሹል/ ነገሮችን ይዞ መገኘት፣

3.4 ለአጉል ሱስ የሚዳርጉ ነገሮችን እንደ ቁማር፣ ጫት፣ አደንዛዥ እጽ፣ ሲጋራ፣ መጠጥ መጠቀምና ይዞ መገኘት/ መተግበር/ ወዘተ

3.5 ፈተና ለመኮረጅ መሞከር፣ መኮረጅ፣ ማስኮረጅ፣

3.6 የት/ቤቱንና የሌሎች ተማሪዎችን ንብረት ማበላሸት፣ ማውደም፣ መስበር፣ መስረቅ ወዘተ፣

3.7 ከተቃራኒ ፆታ ጋር አግባባዊ ያልሆነ ግንኙነት መፍጠር፣

3.8 ሞባይል በትምህርት ቤቱ ግቢ ውሰጥ ይዞ መገኘት ፣

3.9 ከት/ቤት ያለ በቂ ምክንያት መቅረትና ያለፈቃድ ትምህርት አቋርጦ መሄድ፣

3.10 በግድግዳ፣ በሰሌዳ፣ በወንበር፣ በፈተና ወረቀት ወዘተ ፀያፍ ፅሁፎችን መፃፍ ፣

3.11 በክፍል ውስጥ መረበሽ፣ የቤት ሥራ አለመስራትና ለመምህር አለመታዘዝ፣

3.12 ፋሽንን የተከተለ የፀጉር አያያዝ፣ ጌጣጌጦችን መጠቀም፣ ኩል፣ የጥፍር ቀለም፣ የከንፈር ቀለም መቀባትና ማስቲካ ማኘክ ወዘተ፣

## 4. በቅደም ተከተል የሚወሰዱ የከባድ ጥፋቶች ቅጣት

4.1 የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ መስጠትና ወላጅ ማስፈረም

4.2 ከት/ቤት ለተወሰነ ጊዜ ማገድና ወደ ት/ቤቱ ሲመለስ ማስፈረም

4.3 በቀጥታ ከት/ቤት ማባረርና ለሚመለከታቸው ክፍሎች ማሳወቅ፣

4.4 በተበላሹ፣ ለተሰበሩና ለጠፉ ንብረቶች ዋጋቸውን በእጥፍ መክፈል፡፡

## 5. ያለቅደመ ማስጠንቀቂያ በቀጥታ የሚያባርሩ ጥፋቶች

5.1 በት/ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ በግልም ሆነ በቡድን ፀብ፣ረብሻ፣ድብድብ መፍጠር ወዘተ፣

5.2 በት/ቤቱ የሚገኙ ተማሪዎችን፣ ሠራተኞችንና መምህራንን መደባደብ፣ መሳደብ ወጥም ማንጓጠጥ፣ ወዘተ፣

5.3 ከትምህርት መሳሪያ ውጪ ሰለታም /ሹል/ ነገሮችን ይዞ መገኘት፣

5.4 ለአጉል ሱስ የሚዳርጉ ነገሮችን እንደ ቁማር፣ ጫት፣ አደንዛዥ እጽ፣ ሲጋራ፣ መጠጥ መጠቀምና ይዞ መገኘት/ መተግበር/ ወዘተ፣

5.5 የትምህርት ቤት አጥር ዘሎ ወይም ሾልኮ መግባት ወይም መውጣት፣

5.6 በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ የፖለቲካም ሆነ የኃይማኖት ተግባራት ማካሄድ፡፡

እኔ ______________________________ በዚህ ፎርም የተጠቀሰው ተማሪ ወላጅ /አሳዳጊ/ የሆንኩ ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን የት/ቤቱን ደንብና ሰርዓት አንብቤና ተረድቼ ልጄ ስርዓቱንና ደንቡን ባለመጠበቁ ት/ቤቱ በሚወስደው ማንኛውም የዲሲፕሊን ዕርምጃ የተስማማሁበትና ት/ቤቱም በጠራኝ ጊዜ በአፋጣኝ እንደምገኝ በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ሙሉ ስም ______________________________ ፊርማ ______________